# ቅዱስ ዮሐንስና ልጆች

*ከሥርጉተ ሥላሴ*
*መስከረም 2001 ዓ.ም.*

ልጆች ቅዱስ ዮሐንስ ከሁሉም በዓላት ይበልጣል። ታላቁ ዓቢይ የኢትዮጵያ ሀገራችን ዐውደ ዓመት ነው። ምክንያቱም አሮጌው ዓመት አልፎ በአዲስ የተስፋ ዓመት ስለሚተካ ነው።

ልጆች በሀገራችን በኢትዮጵያ ወላጆቻችን ለእኛ ለልጆቻቸው አዲስ ልብስ፣ አዲስ ጫማ የሚገዙልን በቅዱስ ዮሐንስ ስለሆነ በዓሉን በጣም እንወደዋለን። በጣምም እንናፍቀዋለን። እንዲሁም በቅዱስ ዮሐንስ ልዩ ዝግጅት ስለሚኖር ደስ ይለናል። ሥጋም አለ፣ ድፎ ዳቦም አለ፣ ሙልሙልም አለ፣ ቆሎም አለ፣ ሻይ አለ፣ በዚህ ሁሉ ምክንያት ቅዱስ ዮሐንስ የልጆች ልዩ ደስታ ቀን ነው።

በዋዜማው በገጠር የሚኖሩ የገበሬ ልጆች አደይ አበባ ቆርጠው ያዘጋጃሉ። በከተማ የሚኖሩት ደግሞ የአበባ ስዕል ይስላሉ። በቅዱስ ዮሐንስ ዕለት በጧት ልጆች ይነሱና ለወላጆቻቸው፣ ለታላላቅ እህቶቻቸውና ወንድሞቻቸው፣ አክስትና አጎቶቻቸውና ለጎረቢቶቻቸው በየቤታቸው እየሄዱ እንቁጣጣሽ በማለት አበባውን ወይንም የስዕሉን ስጦታ ያበረክታሉ። ስጦታ የተቀበሉት ደግሞ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት አቅፈው በመሳም ደብተር፣ እስክርቢቶ፣ እርሳስ፣ ከረሜላ ወይም ሳንቲም ይሰጧቸዋል። ልጆች በሳንቲሙ ፊሽካ፣ ፊኛ ወይም ደስ ያላቸውን መጫወቻ ገዝተው ይጫወቱበታል።ልጆች ይህ ትልቁ የሆነ ባህላችን ነው።

ከሁሉም ዓመት በዓል የኢትዮጵያ ልጆች የምንወደው ቅዱስ ዮሐንስን ነው። ቅዱስ ዮሐንስ የልጆች የደስታ ቀን፣ የልጆች የሳቅ ቀን እና የጨዋታ ቀን ሲሆን የልጆች ዓመት በዓል ነው ማለት ይቻላል። ቤተሰቡ በሙሉ፣ ጎረቢቱ በሙሉ፣ ልጆችም ሁሉ በአንድ ላይ ሆነው እንደ ባህላችን እየተበላ፣ እየተጠጣ፣ መዝሙር እየተዘመረ፣ ዘፈን እየተዘፈነ ደስ በሚል ሁኔታ በዓሉን እናሳልፋለን።

**መ ል ካ ም  አ ዲ ስ  ዓ መ ት  ይ ሁ ን ል ን : :**

**እ  ን  ቁ  ጣ  ጣ  ሽ  ! ! !**